፲፮ ወውእቱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወእግዚአብ
ሔር አቡነ ዘአፍቀረነ ወወሀበነ ፍሥሐ ዘለዓለም
ወተስፋ ሠናየ በጸጋሁ ።
፲፯ ውእቱ ያስተፍሥሕክሙ ልበክሙ ወያፅንዕክሙ
በኵሉ ምግባር ወበኵሉ ቃል ሠናይ ።

ምዕራፍ ፫ ፤

## ክፍል ፫ ፡ ዘከመ ይደሉ ጸልዮ እምድኅነተ ሰብአ እኩያን ።

፩ ወይእዜኒ አኀዊነ ጸልዩ ለነ ከመ ይሩጽ ቃለ እግዚ
አብሔር ወይሰባሕ በከመ በኀቤክሙ ።

፪ ወከመ ንድኃን እምሰብእ እኩያን ወዐላውያን እስመ
አኮ ኵሉ ዘየአምን ።
፫ ወእግዚአብሔርሰ ምእመን ወጻድቅ ዘያጸንዐክሙ
ወየዐቅበክሙ እምኵሉ እኩይ ።

፬ ንትአመነክሙ ምስለ እግዚአብሔር ከመ ትግበሩ
ዘአዘዝናክሙ ወገበርክሙሂ።

፭ ወእግዚእነ ያርትዕ ልበክሙ ውስተ ፍቅረ እግዚ
አብሔር ወውስተ ተስፋሁ ለክርስቶስ ።

## ክፍል ፬ ፡ ዘከመ ይደሉ በሊዕ በተቀንዮ ።

፮ አኀዊነ ንኤዝዘክሙ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ተገኅሥዎሙ ለኵሎሙ ቢጽ እለ የሐውሩ በት
ምይንት ወአኮ በሥርዐት ዘሠራዕናሆሙ ።

፯ ለሊክሙ ተአምሩ ከመ ርቱዕ ትትመሰሉነ ከመ
ኢሰሳዕነ ላዕሌክሙ ።

፰ ወኢበላዕነ እክለ ባዕድ በከንቱ ዘእንበለ ዳእሙ ወን
ሠርሕ መዓልተ ወሌሊተ ወንትጌበር ከመ ኢናክ
ብድ ላዕሌክሙ ።
፱ ወአኮሰ ዘኢኮነ ብዉሐነ ዳእሙ አርአያ ከመ ንኩን
ክሙ ከመ አንትሙ ትትመሰሉነ ።

፲ ወአመሂ ሀለውኩ ኀቤክሙ ዘንተ አዘዝኩክሙ ዘኢ
ይፈቅድ ይትቀነይ ኢይሴሰይ ።
፲፩ ሰማዕነ ከመ ቦ እምውስቴትክሙ እለ የሐውሩ በሁ
ከት ወአልቦ ዘይትቀነዩ ዓዲ መስተሐውራን ።

፲፪ ወለእለ ከመዝ ንኤዝዞሙ ወንጌሥፆሙ በስሙ ለእግ
ዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ በየውሃት ወበጽምው
ይትገበሩ ተግባሮሙ ወይሴሰዩ ሲሳዮሙ ።
፲፫ ወአንትሙሂ አኀዊነ ኢትትሀከዩ ገቢረ ሠናይ ኵሎ
ጊዜ ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቸርነቱ የወደደን ፲፮
የዘለዓለም ደስታንና እውነተኛ ተስፋን የሰጠን አባ
ታችን እግዚአብሔር እሱ ። ፩ ዮሐ፡ ፬ ፲ ።
ጸጋውን ሰጥቶ ልባችሁን ደስ ያሰኛችሁ በፍጹም ፲፯
ምግባር በበጎ አነጋገር ያጽናችሁ ። ፩ ተሰ፡ ፫ ፲፫ ።

ምዕራፍ ፫ ።

## ክፍል ፫ ፡ ከክፉ ሰዎች ለመዳን መጸለይ እንዲገባ ።

አሁንም ወንድሞቻችን! የእግዚአብሔር ቃል ከእና ፩
ንተ እንደ ደረሰ እንዲሁ ከሁሉ ዘንድ እንዲደርስ
ጸልዩልን ። ቈላ፡ ፬ ፫ ።
ከክፉ ሰዎችና ከከሐዲዎች እንድን ዘንድ፡ ሁሉ በእ ፪
ግዚአብሔር የሚያምን አይደለምና ።
ከክፉ ሁሉ የሚጠብቃችሁና የሚያፀናችሁ እግዚ ፫
አብሔር ግን የታመነ እውነተኛ አምላክ ነው ።
ማቴ፡ ፮ ፲፫፡ ፩ ቆሮ፡ ፩ ፱፡ ፲ - ፲፫ ።
ከእግዚአብሔር ጋር ያዘዝናችሁን እንደምታደርጉ ፬
እንታመንባችኋለን ከዚህ በፊትም አድርጋችኋል ።
፪ ቆሮ፡ ፯ ፲፯፡ ገላ፡ ፭ ፲ ።
ጌታችንም ልቡናችሁን እግዚአብሔርን ወደ መው ፭
ደድና ወደ ክርስቶስ ተስፋ ያቅናው። ፩ ነገ፡ ፰ ፶፰።

## ክፍል ፬ ፡ ሠርቶ መብላት ስለሚገባ ።

ወንድሞቻችን! በሠራንላቸው ሥርዓት ያይደለ በተ ፮
ንኰል የሚሄዱትን ሰዎች ሁሉ ተለዩዋቸው ብለን
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛችኋለን ።
ማቴ፡ ፲፰ ፲፯፡ ሮሜ ፲፮ ፲፯፡ ቲቶ፡ ፫ ፲ ።
እኛ በእናንተ ላይ እንዳልሳሳን ሁሉ እናንተም እኛን ፯
ትመስሉን እንዲገባ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ ።
፩ ቆሮ፡ ፬ ፲፮፡ ፩ ተሰ፡ ፩ ፮ ።
እናንተን እንዳናስቸግር በመዓልትም በሌሊትም ፰
ሠርተን የደከምንበትን እንጂ የሌላውን እህል በከ
ንቱ አልበላንም ። ፩ ቆሮ፡ ፬ ፲፪ ።
ግን የማይገባን ሆኖ አይደለም እናንተ ትመስሉን ፱
ዘንድ አብነት እንድንሆናችሁ ነው እንጂ። ማቴ ፲ ፲፡
፩ ቆሮ፡ ፬ ፲፮ ።
ከእናንተም ዘንድ በነበርኩ ጊዜ ይህን አዝዣችኋለሁ ፲
ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብዬ ። ዘፍጥ፡ ፫ ፲፱ ።
በመካከላችሁ በማወክ የሚኖሩ የሚሠሩት የሌላቸው ፲፩
በዚያውም ላይ ነገር አዋሳጆች እንዳሉ ሰምተናል ።
ኢሳ፡ ፶፮ ፲ ።
እንደነዚህ ያሉትን በቅንነት በፀጥታ እየሠሩ ምግባ ፲፪
ቸውን እንዲመገቡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እንመክራቸዋለን እናዝዛቸዋለን ። ሮሜ ፲፪ ፲፩።
ወንድሞቻችን! እናንተም ሁል ጊዜ በጎ ሥራ መሥ ፲፫
ራትን ቸል አትበሉ ። ገላ፡ ፮ ፱ ።

፲፬ ወእመበ ዘኢይትኤዘዝ ለቃልክሙ ወለመጽሐፍክሙ
ይትፈለጥ ወኢትትሀወልዎ ከመ ይትኃፈር ።
፲፭ ወከመሰ ጸላኢ ኢትረስይዎ አላ ገሥፅዎ ከመ እኁ
ክሙ ።
፲፮ ወውእቱ እምላከ ሰላም የሀብክሙ ሰላመ በኵሉ
ጊዜ ወበኵሉ ግብር፡ ወእግዚእነ የሃሉ ምስለ ኵል
ክሙ ።
፲፯ ዘንተ አምኃ ዘጸሐፍኩ ለክሙ በእዴየ አነ ጳውሎስ፡
ወዝንቱ ትእምርትየ ውስተ ኵሉ መጻሕፍትየ ከመዝ
እጽሕፍ ።
፲፰ ጸጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሃሉ ምስለ
ኵልክሙ ፡ አሜን ።

ተፈጸመት ክልእት መልእክት ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ
ወተጽሕፈት በሎዶቅያ ወተፈነወት በእደ ጢኪቆስ ።
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።



ለቃላችሁና ለመጽሐፋችሁ የማይታዘዝ ቢኖር ይለይ ፲፬
እንዲያፍር አትቀላቀሉት ። ማቴ፡ ፲፰ ፲፯ ።
እንደ ጠላት ግን አታድርጉት ወንድማችሁ እንደመ ፲፭
ሆኑ ምከሩት ገሥፁት እንጂ ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲፯ ።
የሰላም አምላክ እርሱ ሁል ጊዜ በሥራው ሁሉ አን ፲፮
ድነቱን ይስጣችሁ፡ ጌታችን ከሁላችሁ ጋር ይኑር ።
ሮሜ ፲፭ ፴፫፡ ፲፮-፳ ።
ይህን ሰላምታ በእጄ የጻፍኩላችሁ እኔ ጳውሎስ ፲፯
ነኝ፡ በመጻሕፍቶቼ ሁሉ ምልክቴ ይህ ነው እንዲህ
እጽፋለሁ ። ፩ ቆሮ፡ ፲፮ ፳፩ ።
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ፲፰
ይሁን፡ አሜን ። ፪ ጢሞ፡ ፬ ፳፪ ።

በሎዶቅያ ተጽፋ በጢኪቆስ እጅ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
የተላከችው ሁለተኛዪቱ መልእክት ተፈጸመች ።
ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡ አሜን ።